# የACPS Express 12/1/2022: የሱፐስ ስፖትላይት (Supe’s Spotlight)፣ የዲሴምበር (December) የቪዲዮ መልዕክት

## የ‘ሱፐ ስፖትላይት (Supe’s Spotlight)’: የዲሴምበር (December) የቪዲዮ መልዕክት



በዲሴምበር (December) የ‘ሱፐ ስፖትላይት/Supe’s Spotlight ላይ፣ የACPS ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የሆኑት ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) - ከክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break) አስቀድሞ- ስለ ጤናማነት ሃሳባቸውን-አጋርተዋል። ዶ/ር ኬይ-ዋየት (Dr. Kay-Wyatt) በተጨማሪም - በዕረፍት-ጊዜው ወቅት፣ ቤተሰቦች ጥቅም-ሊያገኙባቸው የሚችሉባቸውን የመገኛ-ምንጮች፤ እንደ የምግብ ማከፋፈያ ድርጅቶች (የማህበረሰብ የምግብ የመገኛ-ምንጭ ጽሁፍን-ተመልከቱ) እና የቀለም-ትምህርት እንቅስቃሴ የሆኑትን እንደ የእኛን የክረምት የዕረፍት-ጊዜ/Winter Break ድህረ-ገጽ አካትተው አጋርተዋል።

## የምግብ የመገኛ-ምንጮች፣ ለACPS እንዲገኙ-ማድረግ



የምግብ-ዋስትናን ማጣት፣ በማህበረሰባችን ውስጥ - በተለይ-ደግሞ ከCOVID-19 ወረርሽኝ በኋላ፣ ስጋት እየፈጠረ የሚገኝ-ነገር ሆኗል። አሌክሳንድርያን ከሚያገለግሉ የአካባቢው የምግብ-መገኛ ምንጭ ድርጅቶች መካከል ‘ALIVE!’ ሲሆን፤ በየወሩ፣ በግምት ወደ 4,000 የሚጠጉ ቤተሰብን - ለፍላጎቶቻቸው ምላሽ-ሲሰጥ ቆይቷል።

ALIVE! ዋና ዳይሬክተር የሆኑት፣ ጄነፈር አየርስ (Jennifer Ayers) እንዳሉት፤ የምግብ እርዳታን የሚፈልጉ ሰዎች ቁጥር - እንደገና እየጨረ ሲሆን፣ ይህም የሆነው በኑሮ-ውድነት፣ በኪራይ ወይም በስራ-ዘርፉ ላይ ባሉት ለውጦች ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል። “ሰዎች - ይህን አስቸጋሪ የሆነን ምርጫ - በቤት-ኪራይ እና በምግብ መካከል መምረጥን እያደረጉ ነው” ብለዋል አየርስ (Ayers)። እነዚህ ቤተሰቦች - ALIVE! ባይኖር ምን-ሊያደርጉ እንደሚችሉ ሲጠየቁ፤ የ‘አየርስ (Ayers) ምላሽ፤ “አላምቅም።” ነበር። በመጨመርም ሲናገሩ፤ ከምግብ-መገኛ ምንጮች ከንውን የሆነው እንደ ALIVE! ዓይነቱ ሳይኖር፤ አንዳንድ ቤተሰቦች ተመጣጣኝ ምግብን ማግኘት እና ቤተሰባቸውን መመገብ አስቸጋሪ ሊሆንባቸው ይችላል።

ALIVE! - ለአካባቢው የምግብ-ማስቀመጫዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የምግብ ወጥ-ቤቶች (meal kitchens) እና በመኪና-ሄደው የሚወሰዱባቸው ወይም በእግር-ሄደው በብዛት-የሚከፋፈሉባቸውን ዝግጅቶች በበርካታ በአሌክሳንድርያ-ዙሪያ በሚገኙ አካባቢዎች ውስጥ ያቀርባል። እነዚህ ዝግጅቶች - አብዛኛውን-ጊዜ በሣምንት አንድ ጊዜ የሚከናወኑ፣ እና በድርጅቱ ድህረ-ገጽ (organization's website) ላይ ተዘርዝረው-ይገኛሉ። አብዛኛው የማከፋፈያ ቦታው - አራት-ቤተሰብ ላለው ቤተሰብ - እስከ አምስት ቀናት በቂ የሆኑ ምግቦችን - እንቁላል፣ ዶሮ፣ አታልክት፣ ወቅቱን-የጠበቁ ምርቶች (seasonal produce) እና ትኩስ-ዳቦን ጨምሮ- ያከፋፍላል። በ'West End Food Hub' ማከፋፈያው ውስጥ፤ ቤተሰቦች ምን ዓይነት ምግብ መውሰድ እንደሚፈልጉ መምረት የሚችሉ እና መሠረታዊ የሆኑ የንጽህና-መጠበቂያ ዕቃዎችን እና ማጽጃ ቁሳቁሶችንም ማግኘት፤ እና ሌሎች የሚያስፈልጓቸውን አገልግሎቶች እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃዎችንም ማግኘት ይችላሉ። የALIVE!' የቤተሰብ እርዳታ ፕሮግራም - በተጨማሪም፣ ከቤታቸው መውጣት ለማይችሉ ቤተሰቦች - እንደ አንድ-ብቻውን የሆነ ወላጅ (single parent) ቤተሰብን የሚያስተዳዱሩ ያሉትን፤ ግሮሰሪዎችን ወደ ቤት-ወስዶ ማከፋፈል ለማድረግ መምራቶች (referrals) ይቀበላል።

የምግብ-ልገሳ መስጠት ሁልጊዜ በALIVE! ውስጥ ተቀባይነት አለው፤ እና አብዛናውን ጊዜ ወቅታዊ-የሆኑ የስራ አይነቶች (seasonal employment) ምክንያት ከጃንዋሪ (January) እስከ ኤፕሪል (April) ባለው ጊዜ ውስጥ - የሚገለገሉ ቤተሰቦች ቁጥር የሚጨምርበት ስለሆነ - የልገሣዎች መጨመር ያስፈልገናል። ኦገስት (August) ወርም እንዲሁ፣ የምግብ-ፍላጎት የሚጨምርበት እና በልገሣ የሚመጡ ደግሞ እንዲሁ የሚቀንስበት ጊዜ ነው። አየርስ (Ayers) እንደተናገሩት፤ በተለይ-የሚፈለጉ ነገሮች፤ ሩዝ፣ ቅመማ-ቅመም (spices)፣ የማብሰያ ዘይት፣ ዱቄት እና የጣሳ ፍራፍሬዎችን የሚያካትት-ነው። ALIVE! በተጨማሪም፤ ልጆች እራሳቸው አሙቀው ወይም እራሳቸው የሚመገቧቸው፤ እንደ ኦትሚል (oatmeal)፣ ግራኖላ ባርስ (granola bars) እና ሴሪያል (cereal) ያሉ ምግቦችን - በልገሣ ቢመጡ የሚያመሰግን-ይሆናል። የገንዘብ ልገሣዎች፤ ትኩስ የሆኑ ነገሮችን - እንደ እንቁላል እና ዶሮ ያሉትን ለመግዛት ይረዳል፤ ይህም ALIVE! የንጥረ-ነገር ሚዛናዊ የሆኑ ምግቦችን እንዲሰጥ ያደርገዋል። በምግብ-ማከማቻው (food warehouse) በሚገኝበት በ801 S. Payne Street ላይ መጥቶ-መስጠት ይቻላል። ALIVE! - የሚለገሱት ዕቃዎች የጠርሙስ-ብልቃጦችን (glass jars)፣ የተከፈቱ የመያዣ ዕቃዎችን፣ ወይም ጊዜያቸው ያለፈባቸውን ምግቦች እንዳይመጡ-ይጠይቃል።

ምግቦችን ለማከፋፈል እና ለመደርደር እና ለምግብ ማከፋፈል ዝግጅቶች ለመርዳት፤ ALIVE! የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (Volunteers)ን በደስታ-ይቀበላል። "ይህ በእውነት ከALIVE! ጋር በቀላሉ የመሳተፍ እና ጎረቤታችሁን የምታገለግሉበት ኢጋጣሚ-ነው" ብለዋ አየርስ (Ayers)። በALIVE! ውስጥ - የምግብ እርዳታን የሚያገኙ አንዳንድ የማህበረሰብ አባላቶች - የበጎ-ፈቃድ ሠራተኛም (volunteer) ናቸው።

ALIVE! ወርሃዊ የምግብ ማከፋፈያ የጊዜ-ሰሌዳን እና በALIVE! ውስጥ የተወሰኑ-ሰዓቶችን ያቀርባል። West End Food Hub at 510 S. Van Dorn Street. ለዲሴምበር (December) የተስተካከለ የጊዜ-ሰሌዳን ለማግኘት፤ alive-inc.orgን ጎብኙ። ALIVE! የአሌክሳንድርያ ማህበረሰብን በተለያዩ ሌሎች መንገዶች እንዴት እንደሚረዳ ለማወቅም-ከፈለጋችሁ፣ በድህረ-ገጹ ወይም በፌስ-ቡክ፣ ኢንስተግራም/Instagram ወይም ትዊተር/Twitter ላይ ማግኘት-ትችላላሁ።

በተጨማሪም፤ በአካባቢው የምግብ አቅራቢዎች መካከል ስለተቀናበረ ጥረቶች የበለጠ ለማወቅ እና የአሌክሳንድርያ ከተማ የምግብ እርዳታ የመረጃ-ምንጮች ፕሮግራም ማውጫ እና የጊዜ-ሰሌዳን - በHunger Free Alexandria ላይ አግኙ።

# የክረምት (Winter) የአየር-ጠባይ ውሳኔዎች እና ግንኙነቶች



ወደ ክረምት ወራቶች እየገባን ባለንበት ጊዜ፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (ACPS) - በአካል ተገኝቶ (In-Person) ትምህርት አሰጣጥ ሊካሄድባቸው በማይቻልባቸው ቀናቶች ላይ ዕቅድ አቅዷል። ዕቅዳችንም የሚያካትተው፤ የክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) ሁኔታዎች በሚከሰቱ ጊዜ፤ የማስታወቂያ ሂደቶችን እና የመማር ሂደት መቀጠልን አካትቶ-የያዘ ነው። ግባችን፣ ማንኛውም የወደፊት ትምህርት ቤቶች መዘጋት በሚያስፈልጋቸው ቀናቶችን ጠብቀን እያለን፣ የመማር ሂደቱ እንዲቀጥል ማገዝ ነው። በክረምት የአየር ጠባይ ምክንያት - የተዘጋው የመጀመሪያው የትምህርት ቀን በርቀት (virtual) መደበኛ-ባልሆነ መንገድ (asynchronous) የሚሰጥ የትምህርት-አሰጣጥ ሊሆን እንደሚችል፤ ይህም ተማሪዎች አንድ-ዓይነት የሆነውን ማቴሪያል መማር የሚያስችላቸው ሲሆን፣ ነገር ግን - በተለየ ጊዜያቶች እና ቦታዎች ላይ - በቀጥታ-ከሚሰጥ የትምህርት አሰጣጥ ውጪ በሆኑ መልኩ የሚሰጥበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል - ቤተሰቦች፣ ዝግጅት-ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። ትምህርት ቤቶች ከአንድ-ቀን በላይ መዘጋት-የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፤ ተጨማሪ መረጃዎችን የምናጋራችሁ ይሆናል። ተማሪዎች መደበኛ-ባልሆነ መንገድ (asynchronous) ትምህርት በርቀት (virtual) መማር ውስጥ በእያንዳንዱ የትምህርት ቤት ደረጃ ውስጥ እንዴት መካፈል እንደሚችሉ ተጨማሪ-ዝርዝሮችን ለማግኘት፤ እባካችሁ የእኛን የክረምት (winter) የአየር-ጠባይ ግንኙነቶች ድህረ-ገጻችንን ጎብኙ።

## የክረምት-ወቅት የአየር-ጠባይ ሁኔታዎችን - መገምገም

የክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) በሚከሰት-ጊዜ፤ — እንደ በረዶ፣ አይስ/ice ወይም ከመጠን በላይ ቀዝቃዛ የአየር-ጠባይ— በሚከሰት-ጊዜ፣ እና አውቶቡሶችም ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት በደህንነት የመንቀሳቀስ ሁኔታ ሳይኖራቸው ሲቀር፤ ACPS የትምህርት ቤት ህንፃዎችን መዝጋት የሚያስፈልገው እና የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥም በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት በመኖሪያ ቤት ውስጥ ይካሂዳል። በተጨማሪም፤ ወደ ትምህርት ቤት በእግራቸው ለሚመጡ - ወደ ትምህርት ቤት መምጣቱ ደህንነታቸው-ሊጠብቅ የማይችል ከሆነ፤ ወይም ለሠራተኞች ለመጓጓዝ አደገኛ ከሆነ፤ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ የሚሰጥ የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ ለማካሄድ ውሳኔ ይደረግ-ይሆናል። በክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) ሁኔታዎች ወቅት ትምህርት ቤቶችን ለመዝጋት ስንመለከት፣ የተማሪዎቻችን እና የሠራተኞቻችን የደህንነት ሁኔታ፣ የእኛ ቁጥር አንድ ቅድሚያ የምንሰጠው-ጉዳይ ነው። ስለ መንገድ ሁኔታዎች ከአሌክሳንድርያ ከተማ የአስቸኳይ ጊዜ ቁጥጥር ሰራተኞች ጋር በመሆን፤ የመንገዶችን ሁኔታ እና የሕዝብ በእግር-መሄጃች ሁኔታዎቻቸውን ለመገምገም፤ የትምህርት ቤት ሠራተኞችም - የአውቶቡስ የመጓጓዣ መስመሮችን ደህንነት፣ የACPS የመኪና ማቆሚያዎች እና የአውቶቡስ መስመሮች በተመለከተ ግምገማ-በማድረግ ላይ፣ በጥምረት እንሰራለን።

ቤተሰቦች እና ሠራተኞች ቀደም-በልው ዝግጅቶችን ማድረግ እንዳለባቸው በማሰብ፤ ACPS፣ የትምህርት ቤት መዘጋት ውሳኔዎችን ከክረምት የአየር-ጠባይ ሁኔታው ከሚኖርበት ቀን በፊት ባለው ምሽት ለማሳወቅ ሙከራ ያደርጋል። ሆኖም ግን፤ በአየር-ጠባይ ትንበያ ዙሪያ በሚኖሩ በርካታ የማይታወቁ-ነገሮች ምክንያት፤ የመጨረሻውን የጠዋት ትንበያውን እና የመንገድ ሁኔታ አዲስና ማሻሻያ (update)ን ከአሌክሳንድርያ ከተማ የአስቸኳይ-ጊዜ ቁጥጥር (City of Alexandria emergency management) ሠራተኞች እስከሚሰጠን እንጠብቃለን። ሊፈጠር በሚችለው የአየር-ጠባይ ሁኔታ ቀድሞ ባለው ምሽት ውሳኔውን ለማሳወቅ በማንችል ጊዜ፤ ጠቅላይ ስራ አስኪያጁ - የትምህርት ቤት ህንፃዎች መዘጋት አለመዘጋት ውሳኔውን እና በመኖሪያ ቤት የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ ለተማሪዎች መሰጠቱን፣ በግምት ወደ 5:00 a.m. ላይ ያሳውቃሉ። በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን፤ በACPS ድህረ-ገጽ እና ‘ParentSquare’ አማካኝነት፤ ቤተሰቦች እና ሠራተኞች መደበኛ አዲስና ማሻሻያዎች (updates)ን ያገኛሉ።

## ለ'በመኖሪያ-ቤት የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ' መዘጋጀት

በክረምት የአየር-ጠባይ ወቅት (winter weather season) እንደመደበኛ ልምድ-ሆኖ መደረግ ያለበት፤ በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ፣ ተማሪዎች ኮምፒውተሮቻቸውን/ዲቫይሶቻቸውን (computers/devices) እና የመማሪያ ቁሳቁሶቻቸውን ወደ መኖሪያ ቤታቸው እንዲወስዱ በእጅጉ-ይመከራሉ። ይህ፤ በበክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) ምክንያት ትምህርት ቤቶች መዘጋት ሲኖርባቸው፤ ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸው ቁሳቁሶች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው። የመጀመሪያው የርቀት (virtual) መማር ቀን፣ በመደበኛ-ባልሆነ የትምህርት አሰጣጥ (asynchronous) በኦንላይን-የሚከናወን ሲሆን፤ ይህም፣ ተማሪዎች አንድ-ዓይነት ይዘቶች/materialን ለመማር፣ ነገር ግን - የቀጥታ (live) የትምህርት አሰጣጥ ሳይኖር - በተለያየ ጊዜያቶች እና ቦታዎች ላይ በመሆን፣ [በክረምት የአየር-ጠባይ/winter weather የግንኙነቶች ድህረ-ገጾችን](#) ላይ በተገለጸው-መሠረት እንዲማሩ የሚያደርጋቸው ነው። ትምህርት ቤቱ በአካል ተገኝቶ (In-Person) ትምህርት ለመስጠት ከአንድ ቀን-በላይ የሚዘጋ ከሆነ፣ ስለ ርቀት (virtual) ትምህርት አቀማመጥ - ለቀጣዮቹ ቀናቶች የሚኖረውን አዲስና-ማሻሻያ (update)፣ ቤተሰቦችን የሚያገኙ-ይሆናል።

## ከቤተሰቦች እና ሠራተኞች ጋር የሚደረግ ግንኙነት

ከክረምት የአየር-ጠባይ ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤት በሚዘጋ-ጊዜ፤ ቤተሰቦች እና ሠራተኞች - በኢሜል እና በ'ParentSquare' አማካኝነት፣ ማስታወቂያን ያገኛሉ። ይህ መረጃ፤ መደበኛ የክንውን-እንቅስቃሲው እስከሚቀጥል ድረስ - እንደተለጠፈ (post እንደተደረገ) ይቀጥላል። በተጨማሪም፤ የACPS ድህረ-ገጽ፣ አጣዳፊ መስመር (hotline) እና የማህበራዊ ሚዲያ (social media) አውታሮች፤ ተገቢ-የሆነውን የመረጃ ማንቂያ (alert) የሚያካትቱ፤ እና 'ACPS'ም፣ ከክረምት የአየር-ጠባይ ጋር የተያያዙ መዘጋቶችን በአካባቢው የዜና ማሰራጫዎች እና በማህበረሰብ አጋርነት-አማካኝነት የከትምህርት በኋላ የትምህርት-አሰጣጥን በሚሰጡ እና/ወይ በልጅ-እንክብካቤ (Child Care) በኩል፤ መረጃውን ያጋራል። የACPS ትምህርት ቤቶች ዝግ-ሲሆኑ፤ የከትምህርት በኋላ (after-school) እና የልጅ-እንክብካቤ ሰጪዎች (childcare providers) ጋር ስለ የስራ-ክንውናቸው - አንዳንድ አገልግሎት-ሰጪዎች ከተለመደው የትምህርት ቤት ቦታ ውጪ አገልግሎቶችን ሊሰጥ ስለሚችሉ፤ ከእነርሱ-ጋር በቀጥታ ያለውን-ሁኔታ እንዲያረጋግጡ ለቤተሰቦች እናበረታታለን። ሁሉም የ'ACPS' ሠራተኛ እና ቤተሰቦች የክረትም የአየር-ጠባይ ማስታወቂያዎችን እና አዲስና ማሻሻያዎች (updates) ወዲያውኑ ከትምህርት ቤቱ ክፍልኡ/division እንደተላኩ ለማግኘት እንዲችሉ [የ'ParentSquare አፕ/app'ን ዳውንሎድ](#) እንዲያደርጉ እንመክራለን።

## የክረምት የአየር-ጠባይ - ጤናማነት፤ ለACPS ቤተሰቦች



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የትምህርት ቤት ጤና አገልግሎቶች ዳይሬክተር - ሮቢን ዋሊን (Robin Wallin) ሪፖርት-ባደረጉት መሠረት፤ በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ በጉንፋን፣ የመተንፈሻ ቫይረሶች፣ እና በኢንፍሉዌንዛ (influenza ("flu") ሕመም-የታመሙ - ተማሪዎች እና ሠራተኞች ቁጥር መጨመሩን እየተመለከትን ነው።

በዚህ ፍሉ (flu)-መሰል በሽታ የታመሙ ልጆች፤ ሣል እና የተንፈሻ-አካል መተፋፈን (congestion) ያላቸው፣ እና ትኩሣት፣ ብርድ-ብርድ ማለት፣ የጉሮሮ ቁስለት፣ ራስ-ምታት፣ የሰውነት-መቆረጣጠም፣ እና ድካም-መሰማት ሊኖራቸው-ይችላል። በተጨማሪም፤ በበዓላት ጊዜ ወቅት፣ የበለጠ-ጊዜ በቤት ውስጥ (indoors) በማሳለፍ - የእነዚህ ቫይረሶች መተላለፊያ-የአደጋ መጠን ከፍ-ያደርገዋል።

ከበዓላት-በኋላ ወደ ትምህርት ቤት በመመለስ ጊዜ፣ የCOVID-19 ምርመራን-ማድረግ፤ የCOVID-19ን በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ መዛመትን ለመከላከል ሊረዳ-ይችላል። ቤተሰቦች፤ እነዚህን ምልክቶች ልጃቸው ያለው ከሆነ፤ እባካችሁ - ልጁን ወደ ትምህርት ቤት እንዳትልኩት እንጠይቃችኋለን። በትምህርት ቤት ውስጥ - ማንኛውም ትኩሳት ያለው ልጅ - በተሻለ-የጤና ሁኔታ ላይ ሆኖ ወደ ትምህርት ቤት እስከሚመለስ ድረስ፤ በመኖሪያ ቤቱ እንዲያርፍ እና እንዲሻለው የሚላክ-ይሆናል።

በማህበረሰባችን ውስጥ፣ የCOVID-19 ቫይረስ መዛዋወር፤ እየቀጠለ የሚኖርም-ይሆናል። ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሠራተኞች፤ ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሳቸው በፊት - ከህመም-የተነሳ [ማንኛውንም ምልክቶች] የሚያሳዩ-ከሆነ፤ የCOVID-19 ምርመራን እንዲያደርጉ በእጅጉ-እናበረታታለን። ነፃ የ'rapid COVID-19' የምርመራ-ጥቅሎች/test kits፤ ለሁሉም የACPS ቤተሰቦች፣ ከትምህርት ቤት ነርሶች ማግኘት ይቻላል።

ለCOVID-19 ቫይረሱ-እንዳለ (positive) እንደሆነ ተማሪዎ የምርመራ-ውጤቱ የሚያሳይ ከሆነ፤ እባካችሁ - ይህንኑ ውወደ የትምህርት-ገበታ መገኘት ቢሮ (school attendance office) እና፣ ወደ reportingcovid@acps.k12.va.us ኢሜል በማድረግ አሳውቁ። እባካችሁ የሚከተሉትን አስታውሱ:

- ለCOVID-19 በምርመራ ውጤታቸው ቫይረሱ እንዳለ (positive) የሆኑ ግለሰቦች፤ አስፈላጊ-በሆኑት በአምስት-ቀን የመገለያ-ወቅት (isolation period) በሆኑት-ጊዜያት - በትምህርት ቤት ውስጥ ተገኝተው መማር የለባቸውም።
- ተማሪዎች፤ ምልክቶቹ እስከተሻሻሉ-ድረስ እና ለ24 ሰዓታት ምንም የትኩሳት መቀነሻ መድኃኒት ሳይወስዱ - ከትኩሳት-ነፃ ከሆኑ፤ በስድስተኛው ቀን ወደ ትምህርት ቤት ሊመለሱ-ይችላሉ። ከ6-10ኛው ቀን ድረስ፣ ጠበቅ-ብሎ በደንብ የሚይዝ የፊት መሸፈኛ (mask)ን እንዲያደርጉ-ይጠየቃሉ።
- ተጨማሪ-መረጃዎች - ስለ [የ'ACPS' የCOVID-19 መመሪያዎች፤ በኦንላይን-ላይ መገኘት-ይችላል]።

ከተለመዱ የክረምት ህመሞች-እራሳችሁን እና ሌሎችን ለመጠበቅ፤ የሚከተሉት እርምጃዎችን መከተል የሚመከር-ነው:

- ጥሩ የንፅህና-አጠባበቅን፣ ማበረታታት
  - እጆችን በሣሙና እና በውሃ በተደጋጋሚ ማጠብ፤ እና ቢያንስ ለ20 ሰከንዶች - በተለይ-ደግሞ ከታመመ ሰው አካባቢው ከቆያችሁ-በኋላ - መታጠብ።
  - በምታስሉ ወይም በምታስነጥሱ ጊዜ፤ የመጠራረጊያ-ወረቀት (tissue)ን መጠቀም፣ ወይም የክንዳችሁን የላይኛውን-ክፍል - አፋችሁን እና አፍንጫችሁን ለመሸፈን-ተጠቀሙ፤ ነገር-ግን እጆቻችሁን-አትጠቀሙ። የመጠራረጊያ-ወረቀቶቹ (tissues)ን ጣሉ፣ እና እጆቻችሁን ታጠቡ።
- የሕመሙን ስርጭት መቀነስ
  - ከታመሙ-ሰዎች ጋር የቅርብ-ንክኪ ያለው (close contact)–አይኑራችሁ።
  - የታመሙ-ሰዎች፤ ከትምህርት ቤት፣ ከስራ፣ ከትምህርት-በኋላ (after-school) እንቅስቃሴዎች፣ እና ጉዳዮችን ለማስፈጸም-ከቦታ-ቦታ መሄድ (running errands) ከማድረግ-መቆጠብ እና በመኖሪያ ቤት መቆየት አለባቸው።
  - የታመሙ ተማሪዎች ወይም ሠራተኞች፤ ለሙሉ 24 ሰዓታት - ማንኛውም የትኩሣት-መቀነሻ መድሃኒቶችን ሳይወስዱ፣ ከትኩሣት-ነፃ እስከሚሆኑ ድረስ፤ በመኖሪያ-ቤታቸው ውስጥ መቆየት-አለባቸው።
- ክትባት ተወጉ
  - የጉንፋን/flu ክትባትን እና የCOVID-19 ቡስተሮችን/boosters፤ ለቤተሰብዎ ከከፋ የመታመም-አደጋ ሊያደርሰው የሚችለውን አደጋ ለመቀመስ - ከግምት-ውስጥ ማስገባት
  - የጉንፋን/flu ክትባትን እና የCOVID-19 ክትባቶች፤ በበርካታ ፋርማሲዎች፣ ግሮሰሪ ሱቆች፣ የሐኪም ቢሮዎች እና የጤና መምሪያ ውስጥ መገኘት ይችላሉ።
  - ስለ ፍሉ/flu ክትባት - የት መገኘት እንደሚችል በ['CDC' ድህረ-ገጽ] ላይ የበለጠ-መረጃን ማግኘት ይቻላል።

ልጃችሁ ጤናማ ሆኖ መቆየት-እንዲችል እና ሌሎች-እንዳይታመሙ በመከላከል እርዳታ-እንድታደርጉ፤ እናበረታታችኋለን። ስለልጅዎ የጤና ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባክዎን - የልጅዎ የጤና እንክብካቤ ሰጪን  አነጋግሩን።

ጤናማ-የሆነ የበዓል-ወቅት - ለሁላችሁም እንዲሆንላችሁ እንመኛለን!

## የACPS፣ የ‘ESSER III’ ግብረ-መልስ (Feedback) ቅጽ - እስከ ዲሴምበር (Dec.) 11 ቀን 2022 ድረስ፣ ክፍት-ነው



የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - እስከ ዲሴምበር (Dec.) 11 ቀን 2022 ድረስ፤ የባለድርሻ-አባል (stakeholder) አስተያየቶችን ለማግኘት - የትምህርት ቤት ክፍሉ/school division፤ የ‘pandemic relief funds’ን እንዴት መጠቀም-እንደሚችል አስተያየትን-ይጠይቃል። ACPS፣ በ‘American Rescue Plan (ARP) Act Elementary and Secondary School Emergency Relief (ESSER) III የእርዳታ ፕሮግራም’ አማካኝነት፣ የገንዘብ እርዳታን አግኝቷል። የ‘ARP ESSER III Fund’ ዓላማ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንደገና ለመክፈት እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቤት ክንውኖችን ማከናወንን ለመቀጠል፣ COVID-19 በሃገሪቱ ተማሪዎች ላይ ያደረሰውን፣ የቀለም ትምህርት፣ የማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የአዕምሮ-ጤና ፍላጎቶች ላይ ለተከሰቱት ተጽዕኖዎች ምላሽ መስጠት ላይ ለመርዳት ነው።

ይህ እርዳታ፣ COVID-19 ባስከተለው ተጽዕኖ ምክንያት የትምህርት ቤት ህንፃዎች በመዘጋታቸው፣ በተማሪዎች አገልግሎቶች ላይ ምላሽ ለመስጠት የገንዘብ እርዳታ ይሰጣል። ወደ መደበኛው የትምህርት ቤት ክንውኖችም ለመመለስ፣ ዕቅዶችን ለመቅረጽ እና ለማስፈጸምም፣ የገንዘብ እርዳታው ይውላል። ስለ ACPS የፌደራል የፓንዳሚክ ግራንት (federal pandemic grants) የገንዘብ ሪፖርቶች - የበለጠ መረጃዎችን በ‘ACPS’ ድህረ-ገጽ ላይ ተመልከቱ።

ለዚህ ሂደት አንዱ አካል አድርጎ፤ ማህበረሰባችን እርዳታው - እንዴት ተማሪዎችን፣ ሠራተኛን እና የትምህርት ቤት ክንውኖችን ላይ ጥቅም ላይ ሲውል ለማየት እንደሚፈልጉ ለመረዳት፤ የባለድርሻ አባላት (stakeholder) ግብዓት (input)ን ACPS ይጠይቃል። የACPS ማህበረሰብ አባላቶች፤ ያላቸውን አስተያየት የኦንላይን ግብረ-መልስ (feedback) ቅጽን በመጠቀም፤ ይህም ጥቂት-ደቂቃዎችን ብቻ ለማጠናቀቅ የሚወስድ እና እስከ ዲሴምበር (Dec.) 11 ቀን 2022 ድረስ፤ በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ፣ ዳሪ እና አረብኛ መገኘት-በሚችለው ላይ ማስገባት ይችላሉ።

## የACHS - የሴቶች የቫሊቦል ቡድን፣ የ2022 የስቴት ሻምፒዮንሽፕን አሸነፈ



የአሌክሳንድርያ ከተማ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የሴቶች የቫሊቦል ቡድን - በኖቬምበር (Nov.) 19 ቀን 2022 ላይ፣ የ2022 የቫሊቦችል የስቴት ሻምፒዮንሽፕን በ3-2 በሆነ ጨዋታ - ሻምፒዮናውን ይዞ ከነበረው

ከቻርልስ ጄ. ኮልጋን ሲኒየር ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Charles J. Colgan Sr. High School) ጋር ተጫውቶ በማሸነፍ፣ ታሪክን-ሰርተዋል።

ለአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) የሴቶች የቫሊቦል ጨዋታ - ይህ ሁለተኛ የስቴት ሻምፒዮንሸፕ ሆኖ ሳለ፤ ይህ የዲስትሪክት ሻምፒዮንሸፕን፣ የክልላዊ ሻምፒዮንሸፕን እና የስቴት ሻምፒዮንሸፕን በአንድ - 'ACHS' ስም ሲያሸንፍ የመጀመሪያው ቡድን ነው።

በዋና የቫሊቦች አሰልጣኝ በዳኒኤሌ ቶርን (Danielle Thorne) እና በረዳት አሰልጣኞች ጆርዳን ኮክስ (Jordan Cox)፣ ኢቫ ኧርዊን (Eva Irwin) እና ጄሲካ ሌሲ (Jessica Lacy) የተመራው-ይህ ቡድን፤ "ትልቅ-የሆነ ማሸነፍን ለቫሊቦል ፕሮግራሙ ያስገኘ-ቡድን" ብለው፣ የአትሌቲክስ & የተማሪ እንቅስቃሴ ዋና-ስራ አስኪያጅ ጄምስ ፓርከር (James Parker) ተናግረዋል። በመጀመሪያ ዓመት አሰልጣኝነቷ፤ የACPS አሉሙነስ እና የቀድሞ የቫሊቦች ተጫዋች - ቶርን (Thorne)፤ የመጀመሪያ የሴት ዋና አሰልጣኝ ሆና በACHS - የስቴት ሻምፒዮንሸፕ አሸናፊ እንዲሆን አድርጋለች።

"ሙሉ ዙሪያውን ያጠናቀቅን ስሜት-ነው የስቴት ሻምፒዮንሸፕን ማሸነፍ፣" ብለው ገልጸዋል ቶርን (Thorne)። "ምንም እንኳን ይህ የመጀመሪያ አብንረን-የሆንበት ሲዝን/season ብቻ ቢሆንም፤ ከጄሲ፣ ኢቫ እና ጆርዳን ጋር በመስራቴ በጣም ዕድለኛ ያደርገኛል፤ እና በመጪው ዓመታት ውስጥ እንደ-ፕሮግራም ምን ማሳካት እንደምንችል ለማየት በደስታ-ይጠብቃለሁ።"

ቡድኑ ሲዝኑን/season - በ32-2 ሬከርድ የጨረሰ ሲሆን፤ ባለፈው ዓመት - አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ለስቴት ውድድር አልበቃም-ነበር። ፓርከር (Parker) እንዳሉት፤ ቡድኑ መልሰው-እራሳቸውን ለማውጣት መቻላቸውን በዚህ-ዓመት ያሳዩበት እና በግባቸው ላይ ምንም-ተስፋ እንደማይቆርጡ አሳይተዋል።

"ለስኬቱ ዋናው-ቁልፍ ነው ብዬ የማስበው፣ የቡድኑ የስራ ስነ-ምግባት እና የቡድኑ ኬሚስትሪ መኖሩ-ነው፣" ቶርኔ (Thorne) በማስተዋል-ሲናገሩ። "በልምምድ እርስ-በራሳቸውን በየቀኑ ወደፊት እያሳደጉ፤ በሚችሉት መጠን ምርጥ-ለመሆን የሚችሉትን አድርገዋል። እርስ-በራሳቸውንም የሚያበረታቱ የነበሩ እና፣ ለእያንዳንዳቸው ስኬታማነት ሁሉም ደስተኞች ነበሩ።" ፓርከር (Parker) ጨምረውም-ሲናገሩ፤ የቡድኑ የስኬት ፎርሙላ - በመጫወቻ ሜዳው ላይ እና ከዚያ ውጪ ባሳዩት የላቀ-ደረጃ ያለው ቁርጠንነት - የሚገለጽ ነው፤ እና "ቡድናቸውን የማስቀደም-አመለካከት አላቸው!"

## የ'FACE' ማዕከል፤ የሪባን-መቁረጥ ዝግጅትን አክብሯል



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ማክሰኞ፣ ኖቬምበር (Nov.) 29 ቀን 2022 ላይ፣ አዲሱን የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሣትፎ (Family and Community Engagement (FACE) ማዕከልን - በፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ስድስተኛው ፎቅ ላይ መከፈቱን በማስመልከት - የሪባን-መቁረጥ ስነስርዓትን አከናውኗል። ዝግጅቱ፤ የቦታውን መከፈት ለማክበር፣ እንዲሁም የ'FACE' ቡድን በእያንዳንዱ-ቀን የሚያከናውኑትን ስራ ለማክበርም-ጭምር የተዘጋጀ ነበር። የማህበረሰቡ የተከበሩ-ሰዎች እና የተመረቱ ባለስልጣናት ተገኝተው-የነበረ ሲሆን፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ የቦርድ አባላቶች - ታሚ ኢግናሲዮ (Tammy Ignacio) እና ዶ/ር ሚሼል ሪፍ (Dr. Michelle Rief)፣ እንዲሁም-ደግሞ የአሌክሳንድያ ከተማ ካውንስል አባላቶች - ካኔክ አጉኢር (Canek

Aguirre) እና አሊአ ጋስኪንስ (Alyia Gaskins) ጨምሮ-ተገኝተዋል። የACPS ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የሆኑት - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፣ የ‘FACE’ ስራ አስኪያጅ ክሪሽና ሌቫ (Krishna Leyva) እና የትምህርት ቤት ሹም እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች - ጁሊአ በርጎስ (Julia Burgos) - ለተሰበሰበው- እንዲሁም ከ’FACE’ የፕሮግራም-አሰጣጥ ጥቅም-ለአገኙ የቤተሰብ አባላቶችም ንግግር-አድርገዋል።

“እዚህ በአዲሱ የ‘FACE’ ማዕከል ላይ፣ የእኛ ቡድን ለACPS ቤተሰቦች በማዳረስ የሚገልጹት፣ አሁንም በቤተሰቦች ላይ ትርጉም-ሰጪ የሆኑ ዕድሎችን በመቅረጽ የተማሪን የቀለም-ትምህርት ስኬትን እና ጤናማ የማህበራዊ-ስሜታዊነት እድገትን ለመደገፍ ቤተሰቦችን በማሳተፍ እድገቱን ይቀጥላል፣” ብለዋል ዶ/ር ኬይ-ዋየት (Dr. Kay-Wyatt)። “የእኛ የ‘FACE’ ቡድን ጥረት፤ በሁለትዮሽ የግንኙነት መንገዶችን ለማጠንካር፣ ባህላዊ ግንዛቤን እና የቀለም-ትምህርት ስኬታማነት ላይ ለማሳደግ እየሰራ ባለበት ጊዜ፤ የቤተሰብ-የትምህርት ቤት አጋርነቶችን ለማጠንከር ይጥራል።”

የ‘FACE’ ስራ አስኪያጅ ክሪሽና ሌቫ (Krishna Leyva) ሲገልጹ፤ ለዓመታት ያስፈለገ ስራ ወደ ማዕከሉ መከፈት አድርሷል — በወረርሽኙ ምክንያት መዘግየት የነበረ ቢሆንም — እናም-በመጨመር ሲናገሩ፤ “የቤተሰብ ተሳትፎ ፕሮግራም አይደለም፣ ልምድ እንጂ” በማለት - ይህን በአዕምሮአችን ማስቀመጥ ያስፈልጋል-ብለዋል።

በማውንት ቨርነን ኮሚውኒቲ (Mount Vernon Community) ትምህርት ቤት - የቤተሰብ የግንኙነት ክፍል-የሆኑት እና በሕይወት የሚገኙ ታሪክ-ሰሪ የሆኑት፤ ሮዛ ላንደሮስ (Rosa Landeros)፤ እርሳቸውን ያላቸውን አመለካከት ሲገልጹ - ከ25 ዓመታት በላይ በACPS ውስጥ ባላቸው ግልጋሎት - የቤተሰብ-ትምህርት ቤት አጋርነቶችን ቅድሚያ-የሚሰጡት ጠቃሚ-ነገር መሆኑን ተናግረዋል። በአጽንዖት ሲናገሩም፤ ተማሪዎቻችን በቀለም-ትምህርት ስኬት እንዲያገኙ ለመርዳት “ጠቅላላ-ሰፈሩ ያስፈልጋል/takes a village”፤ እና እንዴት አዲሱ የ‘FACE’ ማዕከል ይህን ጠንካራ-የሆነ - የACPS ቤተሰቦችን ለመርዳት የገባውን ቁርጠኝነት ወክሎ እንደሚያሳይ ያላቸውን-ኩራት አጋርተዋል።

‘FACE’ የትምህርት ቤት ክፍሉን ዓላማ ለቤተሰብ ተሳትፎ ለማስፈጸም - በቋንቋ-በልዩ ሁኔታ በተዘጋጀ፣ እና በባለ-ሁለት ቋንቋ የቤተሰብ የግንኙነት ክፍሎች (bilingual family liaisons)፤ በአማራኛ፣ አረብኛ እና ስፓኒሽ ቋንቋን ለሚናገሩ ቤተሰቦችን ለማገልገል የተዘጋጁ-ናቸው። የ‘FACE’ ማዕከል፤ ለእነዚህ የቤተሰብ የግንኙነት ክፍሎች (family liaisons) - እንደ ክፍሉ የስራ-መሠረት በመሆን ከቤተሰቦች እና ማህበረሰቡ ጋር እውነተኛ-የሆነ ግንኙነቶችን ለመገንባት እንዲረዳቸው - እንደ መቀመጫ-ቦታ ሆኖ ያገለግላል። በማዕከሉ ውስጥ፤ አስፈላጊ-የሆኑ የመረጃ-ምንጮችም ለሁሉም የACPS ቤተሰቦች መገኘት የሚችሉ ሲሆን፤ የትምህርታዊ ስኬታማነት የሚረዳ እና በአጠቃላይ ምርጥ-የሆነ ሕይወትን ለማስገኘት፤ ከአውደ-ጥናቶች(workshops) እና ሌላ እንቅስቃሴዎች ጋር በመሆን የሚደግፍ-ይሆናል።

## የ‘ሊንክ (LINK)’ ክለብ - ለACPS ቤተሰቦች፤ ደህንነቱ-የተጠበቀ እና ውጤታማ የሆነ የከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞችን ይሰጣል




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ተማሪዎቻችንን እና ቤተሰቦቻችንን በርካታ-የሆኑ ፍላጎቶች ምላሽ-ለመስጠት፤ የትምህርት ቤታችን ክፍል/division - ቁጥጥር-የሚደረግበት የከትምህርት-

በኋላ (after-school) የፕሮግራም-አሰጣጥን ያቀርባል። የሚገኘው ይህ የፕሮግራም-አሰጣጥ፤ ልጆች አዎንታዊ የሕይወት ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያስፈልጓቸውን ችሎታዎች እንዲያዳብሩ ሊረዳቸው-ይችላል። ከ2018 ጀምሮ፣ ACPS ከፍተኛ-ጥራት ያለው የከትምህርት-በኋላ (afterschool) ፕሮግራሞችን፣ በ‘Linking Instruction Nurturing Knowledge (LINK) ክለብ’ ቦታዎቹ አማካኝነት ሲሰጥ-ቆይቷል። ‘ሊንክ (LINK)’ ክለብ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ የሆነ አካባቢን ውስጥ፣ ተማሪዎች በእጃቸው-ሊያከናውኗቸው በሚችሉ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ በሚችሉበት፣ በትምህርት ቤት ስራዎቻቸው ላይ እርዳታን የሚያገኙበት እና አዲስ ችሎታዎችን እና ፍላጎቶችን የሚያዳብሩበትን ቦታ በማቅረብ ያሳትፋቸዋል።

በዚህ የትምህርት ዓመት በተጀመሩት አራት አዲስ ቦታዎች - ሊንክ (LINK)’ ክለብ - አሁን - ከ800 በላይ ተማሪዎችን ከK-12 ክፍሎች ውስጥ - በ13 ቦታዎች ላይ፣ ስምንት ቦታዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና አምስቱ በማህበረሰብ-መሠረት ያደረጉ ቦታዎች ውስጥ-ሆኖ እያገለገለ ነው። የብቁነት የደረጃ-አሰጣጥ መመዘኛ (eligibility rubric)ን በመጠቀም፣ የማህበራዊ-ኢኮኖሚክ እና የቀለም-ትምህርት ፍላጎቶችን ለእያንዳንዱ አመልካች - በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ቦታ (Site) ውስጥ፣ ከፍተኛ-ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎችን ማገልገልን ለማረጋገጥ - ለመወሰን ይጠቀማል።

በ‘ሊንክ (LINK)’ ክለብ ወቅት፤ የACPS ብቃታቸው-የተረጋገጠ አስተማሪዎች ከተማሪዎች ጋር የሚሰሩ ሲሆን፤ በትምህርት ቀኑ ያገኙትን የማህበራዊ-ስሜታዊነት እና የቀለም ትምህርት አገልግሎቶችን ላይ “link” በከትምህርት በኋላ ሰዓቱ ወቅት በሚሰጡ እርዳታዎቹ በማገዝ የሚሰራ-ነው። ይህ የሚያካትቱት፤ የቀለም-ትምህርት ላይ ማስጠናት/tutoring፣ የቤትስራ እርዳታ፣ በፕሮጀክት ላይ መሠረት ያደረገ ትምህርት እና ማህበራዊ-ስሜታዊነት እርዳታዎች ናቸው። ከዚህ ዓመት ጀምሮ፤ የACPS አስተማሪዎች - የ‘LINKing’ን ወደ ‘Future Club’ በበርካታ ቦታዎቹ ላይ ማስፈጸምን፣ ይህም - ከ‘Project GLAD’ እና ‘Advancement Via Individual Determination (AVID)’ ከሚገኝ ተመራጭ-የሆኑ ልምዶችን በሚያጣምረው - ተማሪዎችን በገጽታዊ ፍለጋ-ላይ ትኩረት አድርጎ ለማህበረሰባዊ ለውጥ ወኪል በሚያደርጋቸው ስራ-ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሳተፉ ያደርጋቸዋል። ተማሪዎች - በተጨማሪም፤ ሣምንታዊ የ‘STEMulation Club’ ያላቸው ሲሆን፣ የየቀኑን አስቸጋሪ-ሁኔታዎች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችሉ መንገዶችን ሃሳብ-በማመንጨት እና መሠረታዊ ጽንሰ-ሃሳቦችን በሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂነሪንግ እና በሂሳብ (science, technology, engineering and mathematics (STEM) ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ ይጠቀሙታል።



የ‘ሊንክ (LINK)’ ክለብ፤ የ‘RULER curriculum’ን በማካተት፤ ለማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) - በማስረጃ-ላይ መሠረት ባደረገ አቀራረብ ላይ - በ2021 የትምህርት ክፍል/division ውስጥ እንዲካተት-በተደረገው ውስጥም፤ አካትቶታል። የ‘RULER’ እንቅስቃሴዎች፤ ተማሪዎች የስሜቶችን ዋጋ እንዲረዱ፣ የስሜታዊ ብልህነት ችሎታዎችን እንዲገነቡ እና አዎንታዊ የሆነ የትምህርት ቤት አኳሃን (school climate)ን እንዲጠብቁ ይረዳል። ተማሪዎች በተጨማሪም፤ በሣምንታዊው የመካሪነት ቡድኖች ውስጥ - በ‘Little Friends for Peace’ እና በ ‘Jireh’s Place’ የተዘጋጀውን - በስራ-ላይ የሚውሉ ችሎታዎች ላይ - የርህራሄ እና ሃዘኔታ ስሜትን ለመገንባት፣ ንዴትን ለመቆጣጠር መቻልን፣ ግጭትን የመፍታት ችሎታዎች እና ኃይልን-የማግኘት አቅም ላይ ለማስተማር የተቀረጸውን - ተግባራዊ ችሎታዎችን የሚማሩበት-ይሆናል። የመካከለኛ (Middle) እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ እንደ ወርሃዊ የአመራርነት አውደጥናት ያሉትን - እንደ-እኩያ-የሆነ ተጠሪ-ተወካዮች ሆነው በአጋርነት፣ ከአሌክሳንድርያ ከተማ የማህበረሰብ እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ (City of Alexandria Department of Community and Human Services) ጋር ሆነው ከሚያገለግሉት - በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች - የተዘጋጀውን፣ ተጨማሪ የሆኑ እገዛዎችን ያገኛሉ። በተጨማሪም፤ ሣምታዊ ክፍለጊዜዎች በሆነው እና በ‘Capital Youth Empowerment’ ፕርግራም በተዘጋጀው - ስለ - የፍቅር-ጓደኝነት

(dating) ጥቃት፣ እና የቤት-ውስጥ ጥቃት ጋር የተገናኙ - አመለካከቶች እና ባህሪያቶች ምላሽ-የሚሰጠውን፤ እና ከግንኙነት ጋር እና ተያያዥ-ከሆኑ አስጊ-ነገሮች ጋር ያሉትን ችግሮች ለመቀነስ እና ኃይል-እንዲኖራቸው ለማድረግ ችሎታዎችን የሚገነባ ነው። በተጨማሪም፤ ከ20 በላይ የሚሆኑ የአካባቢ የንግድ-ድርጅቶች እና የማህበረሰብ ድርጅቶች፤ በርካታ የማበልጸጊያ እንቅስቃሴዎችን - እንደ ሮቦት-ስራ፣ ቼዝ፣ ምግብ-ስራ፣ ዳንስ፣ አርብ እና ቲያትር ያሉትን ጨምሮ፤ ይሰጣሉ።

"በእውነት፤ የእነርሱም-ዓላማ ለአሌክሳንድርያ ወጣት እድገት እና ስኬት አስተዋጽዖ ለማድረግ ከሆኑት የማህበረሰብ አባላቶች እርዳታ ማግኘት በመቻላችን ዕድለኞች ያደርገናል፣" ብለዋይ የACPS ከትምህርት ቤት ውጪ ጊዜ (out-of-school-time) ማናጀርን - ማሪሶል ሞራለስ (Marisol Morales)።

ምርምር (Research) እንደሚያሳየው፤ ጥራት-ያለው የከትምህርት-በኋላ ፕሮግራም አሰጣጥ፣ የማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ የማስተዋል እና የቀለም-ትምህርት ዕድገትን እንደሚደግፍ-ያሳያል። በተጨማሪም፤ ለተማሪዎች ደህንነቱ-የተጠበቀ እና እገዛ-ሰጪ አካባቢን ስለሚሰጥ፣ አስጊ-የሆኑ ባህሪያቶችን ለመቀከስ የሚረዳ-ነው። "ከፍተኛ-ጥራት ያለው የከትምህርት በኋላ ፕሮግራም-አሰጣጥን ካለምንም-ክፍያ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በመስጠት፤ በቀለም-ትምህርት ስኬታማነት ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ክፍተት-ለማጥፋት እርዳታ የምናደርግ ሲሆን፤ በዚያው-ጎን ለጎን ደግሞ ቤተሰቦችን - ልጆቻቸው በሚጠቅማቸው እንቅስቃሴ ውስጥ ከእኩዮቻቸው ጋር ደህንነቱ በተጠበቀ አካባቢ ውስጥ ሆነው መሣተፋቸው ማወቃቸው የሚሰጣቸውን ዕረፍት - ድጋፍ-ሰጪ ይሆንላቸዋል፤" ብለዋል ሻና ሳምሰን (Shanna Samson) - በACPS ውስጥ - የተራዘመ-ቀን፣ ስልታዊ ማነሳሻ እና የፕሮግራም ዕድገት - ረዳት ዳይሬክተር። "ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር ትብብርን በመፍጠር፤ በይበልጥ ለተጋለጡ ተማሪዎቻችን - የእንክብካቤ እጆቻችንን ዙሪያቸው አድርገን - በትምህርት ቤት ውስጥ እና በሕይወት ስኬትማ ሊያደርጋቸው የሚችለውን ዕድል ለማሳደርግ የጠቀረጸውን፣ ሁሉን-አቀፍ የሆነ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ይህ 'ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም/equity for all' በስራ-ላይ ውሎ ሲታይ ነው።"




የACPS - የ'ሊንክ (LINK)' ክለብ - የአገልግሎት ጊዜ ከ3-6 p.m. ከትምህርት ቤት በኋላ - በየቀኑ ሲሆን፤ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ በ40 ሣምንታት ውስጥ እና በበጋ (summer) ወቅት ደግሞ በስምንት ሣምንታት ውስጥ ይከናወናል። አስፈላጊ-ናቸው ተብለው በተለዩት በ[City of Alexandria's Children and Youth Executive Plan] ውስጥ ላሉት ምላሽ-በመስጠት ላይ፤ ፕሮግራሙ፣ በACPS - የማህበረሰብ አጋርነቶች እና ተሣትፎ ቢሮ (Office of Community Partnerships and Engagement) ቡድን - ከበርካታ የACPS መምሪያዎች እና ትምህርታዊ ባለድርሻ-አባላቶች (stakeholders) ካገኘው እገዛ ጋር - በትብብር የተቀረጸ-ነበር።

በአሁኑ-ጊዜ፤ 'ሊንክ (LINK)' ክለብ - የገንዘብ-እርዳታን የሚያገኘው ከU.S. Department of Education 21st Century Community Learning Center፣ Elementary and Secondary School Emergency Relief funds እና በርካታ የፋውንዴሽን ግራንቶች (foundational grants) ነው። ፕሮግራሙ ሊሳካ የቻለው፤ ጠቃሚ-በሆነው አጋርነቶች - ከአሌክሳንድርያ ከተማ የመዝናኛ፣ ፓርኮች እንእ ባህላዊ እንቅስቃሴዎች መምሪያ፣ የ'Alexandria Redevelopment Housing Authority'፣ የ'Community Lodgings and Homes for America' በተደረገ-ትብብርነት ነው። ሊንክ (LINK)' ክለብ - በዓይነት ከተሰጡት ግሩም-የሆኑ እርዳታዎች፣ የተቋም መጠቀሚያ እና የሠራተኞች ቁጥጥርን - ከማህበረሰብ አጋሮቻችን ባይገኙ-ኖሮ ስኬታማ-ሊሆን አይችልም ነበር።

በተመረጡ የ‘ሊንክ (LINK)’ ክለብ ቦታዎች ውስጥ፤ ክፍት-ቦታዎች አሁንም የሚገኙ-ይሆናል። በ‘ሊንክ (LINK)’ ክለብ ውስጥ ልጅዎ እንዲካፈል ፍላጎት ካላችሁ፤ እባካችሁ - የማመልከቻ ቅጹን በእንግሊዘኛ ወይም ስፓኒሽ ሞታችሁ-አጠናቅቁ። ለሚኖረው-ቦታ - ተማሪዎች ሊመረጡ የሚችሉት፤ በቀለም-ትምህርት እና በማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ላይ መሠረት ባደረገ-ሁኔታ ነው። በ‘ሊንክ (LINK)’ ክለብ ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ እባካችሁ ማሪሶል ሞራለስ (Marisol Morales)ን የACPS ከትምህርት ቤት ውጪ ጊዜ (out-of-school-time) ማናጀርን፣ በlinkclub@acps.k12.us አነጋግሩ።

## የተማሪ ሚስጢራዊ የፈተና መዝገቦችን ስለማስወገድ፣ የተሰጠ-ማስታወቂያ



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)፤ የማስረጃ-ስብስብን (የተማሪ የስራ ናሙናዎች) - ከ‘የቨርጂኒያ አማራጭ የግምገማ ፕሮግራም (Virginia Alternate Assessment Program (VAAP)’ በትምህርት ዓመት ከ2014-2015 እስከ ከ2018-2019 ባለው-ጊዜ ውስጥ፣ ከ3-8ኛ እና ከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙ - ያሏቸውን-ስብስቦች፣ የማጽዳት ሂደቶችን በማካሄድ ላይ ነው። ልጅዎ በ‘VAAP’ ውስጥ - በ2014-2019 ውስጥ ተካፍሎ ከነበረ፤ የተማሪ የሥራ ናሙናዎችን፣ ለመሰብሰብ እና ለማስቀመጥ ትችላላችሁ።

መጥቶ-የመውሰጃ ጊዜን ለማመቻቸት፤ እባካችሁ፣ የ‘Department of Accountability and Research’ን በ703-619-8032 አነጋግሩ። መጥታችሁ-ከመውሰዳችሁ በፊት፤ የአምስት-ቀናት ቀድሞ የመሰናጃ-ጊዜን፣ እንድትሰጡን እንጠይቃለን። እስከ ፌብሩዋሪ (Feb.) 3 ቀን 2023 ድረስ፤ መጥታችሁ-ያልወሰዳችሁ ፋይሎች፤ እንዲወገዱ ይደረጋሉ።

## የዲሴምበር (Dec.) 1 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ (Summary)



በዚህ ዲሴምበር (Dec.) 1 ቀን 2022 ስብሰባው ላይ፤ የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ የሚከተሉትን ርዕሶች ላይ ተነጋግሮበታል:

- ለ2023–2024 - ለሁለተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የፕሮግራም ጥናቶች
- የየግል የቤተሰብ እና የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሣትፎ (Family and Community Engagement (FACE) - መርሃ-ግብር ብሉፕሪንቶች (Action Plan Blueprints)፣ ለሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች
- የፖሊሲ ክለሳዎች
- የሠራተኛ ጤናማነት

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

## በኖቬምበር (Nov.) 24 ቀን 2022 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ኖቬምበር (Nov.) 24 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 107.3 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በኖቬምበር (Nov.) 24 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፤ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቃላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።